# የአብዮትና የረሃብ አዙሪት

ክፍል 1     አሥራደው (ከፈረንሳይ)





## መንደርደሪያ:

I. በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን፤

- « የምትወደንና የምንወድህ ሕዝባችን ሆይ ! » እየተባለ፤
- « አባባ ጃንሆይ የኛ እናት አባት፤
  አሳድገውናል በማር በወተት »
- « ኃይለሥላሴ ሃዋርያ፤
  የሰላም መሪ ባለሞያ ».....ወዘተ እያለ በችጋር ረገፈ፤

በዚህ የተነሳ፤

- « በደል ጥቃት ለምደህ አልነሳም ካልከኝ፤
  ቀሚሴን ልኬያለሁ ሱሪህን ላክልኝ : » የሚለው

  የቀድሞ የእተጌ መነን አዳሪ ት/ቤት ሴት ተማሪዎች የትግል ጥሪ :

- በ « አትነሳም ወይ ! አትነሳም ወይ !፤
  የግፍ አገዛዝ አይበቃህም ወይ ! »
  በቃ፤ ተነስ ! በቃ፤ ተነስ !

በሚለው የተማሪዎች ትግል ተጀምሮ እንዲያ እንዲያ እያለ፤ በወሎ ድርቅና ረሃብ ታጅቦ፤ አብዮት ፈነዳ፤ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ተሰናበቱ፤

II. ወታደር ሥልጣን ያዘ፤

- ያለምንም ደም እንከኗ ይውደም፤
  በቀና መንፈስ ኢትዮጵያ ትቅደም፤ ........ብሎ፤ ወደ

- የፍየል ወጠጤ ልቡ ያበጠበት፤
  እንዋጋ ብሎ ለነብር ላከበት፤.....   በሚለው ተተካ :

ከፎካሪው ዓላማ በተቃረነ መልኩ በመጠቀም ተዜመ፤ ተደለቀ፤ .... ከዚያም፤

ዲሞን በዲሞትፈር ! አናርኪስቶች አብዮቱን አይቀለብሱም!
አብዮቱ ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ተሸጋግሯል !........ወዘተ እያለ ቆይቶ ሲጨነግፍ በዚያው በጨንጋፋ ማሕጸን ውስጥ፤ ሌላ የአልባኒያ ሶሻልዝም አቀንቃኝ ተረግዞ፤

III. የወያኔ አብዮት ተወለደ፤

- ከአሁን በኋላ ጠመንጃና መድፍ ተቀጥቅጠው ማረሻ ይሆናሉ! በተባለ ማግስት ሻዕቢያና ወያኔ ሲሰርቁ ሳይሆን፤ ሲካፈሉ ስለተጣሉ በባድመ የጦርነት እልቂት ሆነ፤ ወገኖቻችን እንደ ቅጠል ረገፉ፤ ሃብት ባከነ:: አሁን ማን ይሙት : ምክንያቱ ለኛ የማይነገር ሆኖባቸው እንጂ የበሬ ግንባር በማታክል መሬት ያ ሁሉ ወገናችን ከሁለቱም በኩል ማለቅ ነበረበት ?

- ከአሁን በኋላ ሕዝቦች በቀን ሦስቴ ይበላሉ! ተባለ፤ ሦስቴ ቀርቶ አንዱም ጭንቅ ሆኖ አረፈው::

- ከአሁን በኋላ በቶሎ ከራሳችን ተርፎ ወደ ውጪ እንልካለን! በተባለ ማግስት የልመና አቁማዳ ተይዞ በዓለም ዙሪያ ቀፈፋ ተጀመረ::

- የግልገል ጊቤ ግድብ የሃይል አቅርቦታችንን አሟልቶ ወደ ውጪ እንልካለን! ተብሎ ከበሮ በተደለቀ ማግስት ግድቡ ፍርስርስ ተሰፋውም ፍርክስክስ አለና ሕዝቡን ጨለማ ወረሰው::

- ከአሁን በኋላ አገሩን በዘይት እናጥለቀልቀዋለን! በተባለ ማግስት፤ ሕዝቦች የኑሮ ዘይት እያዳለጣቸው እንክትክት፤ የሚላስ የሚቀመስ ጥፍት፤ አለ
  (በነገራችን ላይ ሕዝቦች የሚለው የነሱ አጠራር የብዙዎች ብዙ በመሆኑ አጸያፊ ሲሆን በሰዋሰዋዊ ብዜት አሕዛብ ነጠላ ሲሆን ሕዝብ ደግሞ ብዙ በመሆኑ ሌላ ብዜት አያሻውም፤ እየተንኳኩ ለማደንቆር ካልሆነ በቀር)

- ሰኳር የጠፋው ገበሬው ሰኳር መላስ ስለጀመረ ነው! ባሉ ማግስት ሰኳር ከከተማ እብስ....ወዘተ እረ ስንቱ !!
  እሳቸውን አይቶ መለስ ከማለት ይልቅ፤ አይቶ አያልቅበት ብለን ብንጠራቸው በይበልጥ ምግባራቸውንና ሰብዕናቸውን ቁልጭ አርጎ የሚያሳይ ይመስለኛል ::

- አሁን ደግሞ፤ የአባይ ግድብ ሕዳሴ ይሉናል! ጉድ እኮ ነው: ዲሪቶ ተለብሶ
አቁማዳ ተሸክሞ እየቀፈፉ ሕዳሴ! « ቂጥ ገልቦ ክንብንብ! » ይላችኋል ይች
ናት:.
እስቲ የዓባይን ግድብ በተመለከተ ጥቂት ጥያቄዎችን እናንሳ፤

1. ለምን የአምስት ዓመት የዕድገትና Transformation እቅድ ውስጥ ሳይገባ ቀረ?
2. ዓባይን የመገደቡ ጉዳይ ለምን አሁን ተነሳ ?
3. ለአቶ መለስ ይችን ሃሳብ ማን ሹክ አላቸው ?
4. በዚህ ጫጫታ የወያኔ ትርፍ ምንድነው ?
5. ለምን ዘርፈ ብዙ የሆነ ግድብ እንዳይሠራ ተፈለገ ?
6. ለምን ሱዳን ጠረፍ ላይ ሄዶ መገንባት አስፈለገ ?
7. ለምን እጅግ ትልቅ ግድብ እንዲሆን ተመረጠ ?....ወዘተ

ቁጥር 3 እና 6 ን ጨረፍ አድርጌ የቀሩትን ለናንተ እተዋለሁ፤ ተወያዩበት !

ቁ.3 የሰሜን አፍሪካና የአረብ አገር አምባ ገነኖችን የመታው ሕዝባዊ አውሎ ንፋስ እንቅልፍ የነሳው እሳቸውንና እሳቸውን መሰል አምባ ገነኖችን ብቻ ሳይሆን በአረብ አገራት ዙሪያዋን የተከበበችው እስራኤልንም ጭምር በይበልጥ አስጨንቋታል፤ በተለይ የግብጽና የእስራኤል የሠላም ስምምነት ይናጋ ይሆናል የሚለው አንዱ ሲሆን፤ ሌሎቹ ደግሞ፤ ግብፆች ከኢራኖች ጋር እያደረጉ ያሉት መቀራረብ፤ ሁለቱ የፍልስጤም ነፃ አውጪ ድርጅቶች በግብጽ አማካኝነት እርቅ ማድረጋቸው.... ወዘተ የእስራኤልን ስጋት ጨምረዋል::

ታዲያ ይህን ስጋት ለማስተንፈስና ግብጽን ተይ የምትሠሪው ሥራ ለኛ አይበጅም ለማለት አማራጭ ሲፈለግ፤ ግብጽን ከአናት ሆና የምታስፈራራ አገር ኢትዮጵያ ተገኘች፤ ፈጥነው እስራኤሎች ለአቶ መለስ ይችን ሹክ ሲሏቸው፤ ዘወትር ባገኙት አጋጣሚ ላይ ቶሎ ፊጢጥ የሚሉት የዘወትር የገጠመኝ ተጠቃሚው አቶ መለስ (opportuniste)፤ አንካሳ ዶሮ ሳትቀድማቸው 20 ዓመት ሙሉ ትዝ ያላላቸውን ኢትዮጵያዊነትና የዓባይን ግድብ እንገንባ፤ አታሞ መደለቅና ማስደለቅ ጀመሩ::

ይቺ የፖለቲካ ቁማር በመጠኑም ቢሆን ለጊዜው የሠራች ይመስላል፤ ግብጾች ጉዳዩ ስላሳሰባቸው መልክተኞች ልከው ከአቶ መለስ ጋር እንዲነጋገሩ በማድረግ፤ የግድቡ ሥራ ለአንድ ዓመት እንዲራዘም ተደርጓል፤ ፤ ይህ ሁሉ ውሳኔ የተደረገው በአንድ ፈላጭ ቆራጩ አቶ መለስ ዜናዊ ብቻ ሲሆን፤ በፓርላማ እንደ በግ አጉረው፤ እሳቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲሳደቡና ሲያንጓጥጡ፤ ለመሳቅ፤ ሲደነፉ ለማጨብጨብ፤ ከድሃው ወገናችን በተሰበሰበ ቀረጥ የደለበ ደሞዝ የሚከፈላቸው የፓርላማ አባል ተብዬዎች የሚያውቁት አንድም ነገር የለም ::
ሌላው አሰቂኝ ድራማ ግብጾች በግንባታው ሥራ እንዲሳተፉ የተጠየቁት ሲሆን፤ ሰንት ዘመን የቅኝ ገዢዎች የዓባይ ውሃ ስምምነት እንዳይለወጥብን እያሉ ሲጮሁ የነበሩ፤ ማን ይሙት ዛሬ ለኛ ቀን አሳቢ ሆነው፤ ለግንባታው ወይስ ለጥፋቱ ሊሳተፉ ?!
ነገሩ ሁላ የአንባ ገነን የጣር የነብስ አውጪኝ ጩኸት ሲሆን፤ በአንፃሩ አሳዛኙ የኢትዮጵያ ሕዝብ የኑሮው ውድነት አልበቃ ብሎት፤ አፍንጫውን እየተሰነገ፤ ለዓባይ ግድብ ገንዘብ አዋጣ መባሉነው ::

ዓባይ እንዳይገደብ የሚፈልግ አንድም ኢትዮጵያዊ እንደማይኖር እርግርጠኛ ነኝ፤ ግን እንደ ብል ከስር ስር ያገኙትን ጭዳ የሚያደርጉ፤ ነቀዞች (ሙሰኞች) አገሪቷን እያነቀዙ ባሉበት፤ አገሪቱ የማፍያዎች መፈልፈያ በሆነችበት ወቅት፤ እንዴት ተደርጎ ይህ ዕቅድ በሥራ ላይ ይውላል?

በተጨማሪ የአቶ መለስን የተለመደ ደባ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየው፤
«እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው» እንዲሉ፤
ካልጠፋ ቦታ ሱዳን ጠረፍ ላይ ሄደው፤ የዓባይን ግድብ ካልገነባን ብለው፤ የኑሮ ውድነት የፈነካከተውን ቁስለኛ ሕዝብ ውጥር አርግርው በመያዝ፤ ቁም ስቅሉን ማሳየታቸው ነው ::
ዓባይ መገንባቱ ባልከፋ፤ « አክሱም ለመሃል አገር ሰው ምኑ ነው?» እንዳሉን ነገ ደግሞ የአባይ ግድብ ለሱዳን እንጂ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ምኑ ነው ቢሉንስ?
እሳቸው እንደሆነ በርበሬ ከመቀንጠስ ይልቅ አገር መቀንጠስ ይቀላቸዋል፤
አያስነጥሳቸው ዓይናቸው አይቀላ::

ታዲያ መጠርጠር ይነሰን? « ያልጠረጠረ ተመነጠረ » እንዲሉ ሆኖ አይደል: ከወታደር አገዛዝ የከፋ: ምንም ቢሆን አይመጣም በማለት: ሕዝብ እጁን ዘርግቶ ቢቀበላቸው ዛሬ ጀርባው ላይ ፊጢጥ ብለው: ለም መሬቱን ለባዕድ እየቸበቸቡ እሱን በችጋር የሚያስለበልቡት::

ከዓባይ ግድብ ከተል አርገው እስራኤሎች ከፍልስጤማውያን ወንድሞቻቸው ለመለየት የገነቡት የሃፍረት ግንብ (Le mur de la honte) ዓይነት በኛና በትግራይ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን መሃል ትልቅ የዘር ግንብ እንዲገነባ በዕቅድ ላይ ሳይሆን ይቀራል?! ጠርጥር እሸቱ ሳይጠጥር !!

*ሰሞኑን ደግሞ ሳር ቅጠሉ ሳይቀር ሽብርተኛ ሆነ ብለው፤ ተሸብረው ያሸብራሉ::*
*ጋዜጠኞች ሽብርተኛ፤ እከሌ ሽብርተኛ፤ እነእከሌ ሽብርተኛ፤ ግንቦት7 ሽብርተኛ፤ ብለው ፈራርጀው ሲያበቁ፤ « የዘመድ ጥል የስጋ ትል » ሆነባቸው መሰለኝ እንደ እንቁላል አቅፎ የፈለፈላቸው* ***ሻዕቢያን*** *በሽብርተኝነት አለመፈረጃቸውን ስንመለከት፤ የአቶ መለስ ዜናዊና የአቶ ኢሳይያስ አፈወርቂ ጥል ለኛ ለማስመሰያ እንጂ ለብቻቸው ቢገናኙ፤ ትከሻ ለትከሻ ተቃቅፈው አጂሃ ከሚአለሃ ከተባባሉ በኋላ ለመቶ አመት የሰጡንን የቤት ሥራ እምን እንዳደረሱት ቁጭ ብለው እየተሳሳቁ እንደሚያወጉ አንጠራጠርም::*
*«ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል» ይሏ ችኋል ይቺ ናት::*
*ለነገሩ አልኩ እንጂ፤ የኛ ሰው ነቄ ነው እንኳን ይችን የዝንብ ጠንጋራ በጨረቃ ነቅሶ ያወጣል ::*

*የሚያሳዝነው፤ ከሚወራው ሁሉ አንዱ እንኳን በተግባር የማይውልባት አገራችን፤ መከረኛው ሕዝብ፤ ኑሮን ለመኖር ሳይሆን፤ ለመከራ የተፈጠረ፤ በስሙ እየማሉና እየነገዱ በጀርባው ላይ የሚያናጥሩበትን ተሸክሞ ጀርባው እንደጎበጠ ወደ መቃብር የሚያዘግም፤ በምድራዊ ገሃነም ውስጥ የሚኖር፤ ያልታደለ የመከራ አምራቾች አስተናጋጅ መሆኑ ነው::*

*በየጊዜው ከ5 እስከ7 ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ መራቡ አሳሳቢ እንዳልሆነ በመቁጠር፤ እንደነሱ አባባል የተለመደ «Normal» መሆኑን የወያኔ ባለስልጣናት ባንድ ወቅት ገልጸዋል፤ እንግዲህ እነዚህ ወገኖቻችን የወያኔ የመለመኛ አቁማዳ ለመሙያ እንደ መያዣ እንዲያገለግሉ የተፈረደባቸው መሆኑን ኢትዮጵያዊ ሁሉ ሊረዳው ይገባል::*

***ወያኔ ለሕዝባችን መራብ ተጠያቂ ነው !*** *በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ፤ እንደ ወያኔ ዘመን ያህል ዕርዳታ የዘነበበት፤ ብድር የተነከርንበት ጊዜ የለም፤ ታዲያ ይህ ሁሉ ሆኖ የረሃብና የእብዮት አዙሪት አላበቃም !*

*በሰለጠነው ዓለም ውሻና ድመት.....እንኳን ተራቡ ተብሎ ለእንስሳት መብት ሲጮህ: በኛ አገር የሰው ልጅ ሲራብ የተለመደ ነው ይባላል :: ............*

*ክፍል 2 ይቀጥላል፤*